PRINTED BY
International & Public
Relations Directorate

JAN
2021



RES Plc የአፍና አፍንጫ
ጭንብል ልገሳ አደረገ

# የኢትዮጵያ
# ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ
# Ethiopian Civil Service University

Monthly Newsletter Vol 17 No.5





## የአሶሳ ከተማ አስተዳደር መዋቅራዊ ፕላን

ECSU Est. 1995

## የርክክብ ሥነ-ሥርዓት









## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ቁርጠኝነት
ሁሌም መማር
ብዝሀነት መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
አሳታፊነት
ተባብሮ መስራት

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## Our Values

Customer Focus
Commitment
Continuous Learning
Welcoming Diversity
Attention to the Disadvantaged
Participation
Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content


ECSU hands over Assosa City Structural Plan — 1

APD Provides training to students — 3

የኢ.ሲ.ሰ.ዩ. በቀጣይ 10 ዓመታት — 4

RES Plc የአፍና አፍንጫ ጭንብል ልገሳ አደረገ — 5



**Editor In -Chife**
Tariku Ayano

**Editors**
Anteneh Demisse
Meley Tekeste

**Photos**
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

**ግራፊክስ እና LAYOUT DESIGN**
Dereje Tesfaye


## የዝግጅት ክፍሉ መልእክት

ለመላው የኢትዮጵያ ሲቪል ስርቪስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብና አጠቃላይ ለተቋማችን ሁለንተናዊ ደህንነት ሲባል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዩኒቨርሲቲውን ካምፓስ የደህንነት ጥበቃ በፌዴራል ፖሊስ አባላት እና በካምፓስ ፖሊሶቻችን አማካይነት በቅንጅት እየተሰራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት በተቋማችን በተስተዋሉ እንዳንድ ክስተቶች የተነሳ የተቋማችን ሰራተኞች ላይ የሚፈጠረውን ስነልቦናዊ ጫና ለመቀነስና የተቋሙን አጠቃላይ ንብረት ከስርቆት ለመከላከል መሆኑን የዩኒቨርሲቲዉ ማኅበረሰብ ሊገነዘበዉ ይገባል፡፡ በመሆኑም መላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለተቋሙ ደህንነት ሲባል ጥበቃውን ከሚያሳልጡት አካላት ጋር በጋራ በመሆን የራሱን ሚና እንዲጫወትና በዩኒቨርሲቲው ካምፓስ ውስጥ የሚያስተውላቸውን አጠራጣሪ ነገሮች ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ የድርሻውን እንዲወጣ ስንል መልዕክታችንን ማስተላለፍ እንወዳለን፡፡

**ዝግጅት ክፍሉ**

# ECSU HANDS OVER ASSOSA CITY STRUCTURAL PLAN

Ethiopian Civil Service University handed over the structural plan of Assosa city, prepared by Center for Urban Management and Transformation Training and Consultancy, to the Assosa City Administration on December 22, 2020 at Hidasse Hall. The handover ceremony was attended by senior officials of Asosa City Administration, top management of the university and experts.



**Professor Fikre Dessalegn**
*Ethiopian Civil Service University President*

In his welcoming speech, Prof. Fikre Dessalegn, Ethiopian Civil Service University president , said Center for Urban Management and Transformation is a strong and active center that is doing a lot of works on urban development. The center has already prepared and submitted structural plan for Gambella city and currently it is preparing a structural plan for Kombolcha town. The center has not only developed new structural plans, but also provided training to improve existing urban setting in different province and effective land management system, Prof. Fikre noted.

He also thanked all the professionals and individuals involved in the project for their efforts and endurance for the successful completion of the project and expressed his firm belief that the city administration will implement the structural plan.

Engineer Biftu Goshu , Head of the Urban Development Sector of Benishangul Gumuz Regional State, on his part expressed his pleasure over the completion of the structural plan, assuring the university community that the plan will be implemented without any delay. He also expressed his great anticipate that the plan solves many problems that exists in the city in relation to the city plan.Besides, he asked unreserved support from the university in the future by further strengthening their relationship.

Ato Gebretinsay Tesfay , Director for Center for Urban management and Transformation, pointed out that the preparation of the structural plan was a very challenging task and explained the problems and challenges encountered during the preparation of the plan and expressed his respect and gratitude to all the experts and professionals who participated in the whole process.



**Ato Gebretinsay Tesfay**
*Director for Center for Urban management and Transformation*

Finally Prof. Fikre Dessalegn handed over the structural plan to Ato Umer Mohammed mayor of the Assosa City Administration.



**Ato Umer Mohammed**
*Mayor of the Assosa City Administration*



**Prof. Fikre Dessalegn**
*Ethiopian Civil Service University president*



**Engineer Biftu Goshu**
*Head of the Urban Development Sector of Benishangul Gumuz Regional State*



**Dr. Waqgari Negari**
*Vice President for Training and Consultancy service*





















# APD PROVIDES TRAINING TO STUDENTS



**Dr. Temesgen Birega**
*Director for the Academic Program Directorate*

Ethiopian Civil Service University Academic Program Directorate organized training for the 2020/21 academicyear students from December 23- 25, 2020 at Abay Hall. The training focused on COVID -19 Directives andCreating psychological readiness to re-start the lesson.





At the opening speech of the training, Dr Temesgen Birega, Director for the Academic Program Directorate,Said this training will help the students to gain clear information about what is expected from them during the COVID-19 Pandemic. It also creates psychological readiness for the students to continue their lesson effectively in the first academic semester. Besides, it helps students to know each other and share their experience and background and create conducive teaching learning environment while they staying in the university compound he underscored.





At the program the university's different directorates including Library and Documentation Directorate,Guidance and Counseling Directorate and Students Service Directorate have briefed the rules and regulations of their respective directorates and requested the students to respect the general rules of the university.

# ኢ.ሲ.ሰ.ዩ. በቀጣይ 10 ዓመታት

***የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የሲቪል ሰርቪሱን አቅም ስፔሻላይዝድ የትምህርት ዓይነቶችን በመቅረጽና በማስተማር፣ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠትና በማማከር፣ ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮችን በማድረግ እንዲሁም በተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በመስጠት የተሰጠውን የፐብሊክ ሰርቪሱን አቅም የመገንባት ተልዕኮ በስፋት ሲወጣ ቆይቷል። ይህን ተልዕኮ ለማሳካትም ስትራቴጂክ ዕቅድን በመንደፍና በየጊዜው ዕቅዶቹን ከፐብሊክ ሴክተሩ ፍላጎት ጋር በማዛመድ ለተልዕኮው ስኬት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል። ቀደም ሲል በተዘጋጀውና በ2012 ዓ.ም የተጠናቀቀው የአምስት አመት (ከ2008 - 2012 ዓ.ም) ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረትም ዩኒቨርሲቲውን ወደራዕዩ የሚያደርሱ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን የተከናወኑ ተግባራትና የተመዘገቡ ስኬቶችም በየደረጃው ግምገማ ሲደረግባቸው ቆይቷል።***

የአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ መጠናቀቅ ተከትሎም ዩኒቨርሲቲው የአስር ዓመት (2013-2022 ዓ.ም) አዲስ ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቶ ተህሳስ 27 እና 28 ቀን 2013ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው ካውንስል ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል። በውይይቱ መክፈቻ ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ እንደገለጹት 2013 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው የሃያ አምስት ዓመቱ ጉዞ ተጠናቆ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት ወቅት ነው ብለዋል። ዩኒቨርሲቲው በሃያ አምስት ዓመት ጉዞው በሀገሪቱ የነበረውን የሲቪል ሰርቫንት የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ ተልዕኮውን ተቀብሎ አቅም የመገንባቱን ስራ በስፋትና በብቃት ተወጥቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው የሀገሪቷ ገጽታ ደግሞ በሌላ ገጽታ ላይ የሚገኝ ሲሆን አጠቃላይ ስነምህዳሩም ከዛሬ ሃያ አምስት ዓመታት በፊት ከነበረው በእጅጉ የተለወጠበት ሁኔታ በመኖሩና ከዚህ ለውጥ ጋር ተያይዞ የፐብሊክ ሴክተሩም ፍላጎት እያደገና እየተለወጠ መምጣቱን የገለጹት ፕሮፌሰር ፍቅሬ በዚህ ፍላጎት ልክና ይህንን ለውጥ በሚመጥን ደረጃ ከፍ ብሎ መገኘትና ተልዕኮን በብቃት መወጣት፤ ተወዳደሪና ተመራጭ ተቋም ሆኖ መገኘት አስፈላጊ መሆኑን አመልክተዋል።

በዚህ መነሻነት የ2013ዓ.ም የስራ ዘመንን ስንጀምር አሰራራችንን ለማደራጀት አዲስ የማሻሻያ ደንብ ተቀርጾ በካውንስሉ ውይይት ተደርጎበት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበ ሲሆን ደንቡን መሰረት ያደረገ ስራዎችን ሊያሳልጥ የሚችል የመዋቅር ማሻሻያም የተዘጋጀ ሲሆን የደንቡን መጽደቅ ተከትሎ ወደስራ የሚገባ ይሆናል። የፐብሊክ ሴክተሩን አቅም መገንባት ብቻ ሳይሆን የብቃት ማረጋገጫ ማዕከል በዩኒቨርሲቲያችን የመትከልና ሰርቲፊኬት የመስጠት ስራ በመሰራት ላይም ይገኛል ብለዋል።

የአስር ዓመቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ በተመለከተም በስትራቴጂካዊ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት ያለው ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ የተዳሰሰ ከመሆኑም ባሻገር በመንግስት የተዘጋጀው አዲስ የአስር ዓመት ዕቅድ፣ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንም አዲስ ፍኖተ ካርታ፣ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ተልዕኮም በአዲስ መልክ ብቃትን መሰረት ባደረገ መልኩ ባለድርሻ አካላትን ታሳቢ በማድረግና ዩኒቨርሲቲው አሁን ያለበትን ሁኔታ እና ወደፊት የት መድረስ እንደሚፈልግ በስፋት በመዳሰስ የተዘጋጀ ስትራቴጂካዊ ዕቅድ መሆኑን የገለጹት ፕሮፌሴር ፍቅሬ በዕቅዱ ላይም በተለያየ ደረጃ በዩኒቨርሲቲው ቦርድም፣ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንም ውይይት ተደርጎበት የተዘጋጀ ሲሆን ስድስት ስትራቴጂክ የትኩረት መስክና አስራ አንድ ግቦች ያሉት ጠንካራ ዕቅድ እንደሆነ አመላክተዋል።

ከዚህ በማስለከተል አጠቃላይ የአስር ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ለካውንስሉ አባላት በአቶ ገብረትንሳይ ተስፋይ የከተማ ማኔጅመንትና ትራንስፎርሜሽንና ስልጠናና ማማከር ማዕከል ዳይሬክተርና የስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ኮሚቴ ሰብሳቢ አማካይነት በዝርዝር ቀርቧል።

በቀረበው ሪፖርት መሰረትም የስትራቴጂያዊ ዕቅዱ የተለያዩ ሃገራዊ የሁኔታዎችን ለአብነት ያህልም በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዘርፍ የታዩ ለውጦችና የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መኖራቸው፤ የሲቪል ሰርቪሱ የሰው ሀብት ልማትና ዘርፉን ለማሻሻል የተሄደባቸው መንገዶችና ያስገኟቸው ውጤቶች፤ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 650/2009 እና በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፍኖተ-ካርታ ላይ የተቀመጡት የትኩረት አቅጣጫዎች በመነሻነት ተጠቅሟል።



**ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ**
*የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት*

የዩኒቨርሲቲውን ነባራዊ ሁኔታ ማለትም ዩኒቨርሲቲው በየጊዜው እያደገና እየሰፋ፤ የሚሰጠውም አገልግሎት በዚያ ልክ በመስፋትና በመዘመን ላይ መሆኑ ፣ የተለያዩ አዳዲስ ፕሮጀክቶችንና የመሰረተ ልማት ስራዎችን በማንቀሳቀስ ላይ መሆኑ እንዲሁም ከምስረታው ጀምሮ በመላ ሀገሪቱ ከ40,000 በላይ ፐብሊክ ሰርቫንቶችን ማስመረቁ፣ ከ177,000 በላይ ሰልጣኞች በተለያዩ የስልጠና መስኮች ማሰልጠኑ፣ በማማከር አገልግሎት ረገድም ለተለያዩ ተቋማት የአሰራር እና ሌሎች ሙያዊ ክፍተቶችን በመለየት (የከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ዝግጅትን ጨምሮ) የማማከር አገልግሎት መሰጠቱ፣ ከ200 በላይ ጥናቶችን በማካሄድ እና ተከታታይ አመታዊ ዎርክሾፖችን በማዘጋጀት ችግሮች እንዲቀረፉ የራሱን አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑ ለዕቅዱ እንደመነሻ ተደርጎ ተወስዷል።



ከዚህም ባሻገር የዩኒቨርስቲው (2008-2012 ዓ.ም) የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች እንደ መነሻ የተወሰደ ሲሆን በዚህም መሰረት በስትራቴጂክ ዘመኑ ሰፋፊ ስራዎችን በመስራቱ ለአብነት ያህል 9,981 ተማሪዎችን ማስመረቅ የቻለና 35,270 ለሚሆኑ የፌደራል፣ የክልል እና የከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቫንቶች በተለያዩ ርዕሶች አጫጭር ስልጠዎች የተሰጠ ሲሆን ለ28 ተቋማት በተቋማዊ መዋቅር ማሻሻያና የስራ ዝርዝር ጥናት እና በከተሞች የመዋቅራዊ ፕላን (ማስተር ፕላን) ላይ የማማከር አገልግሎት ፣ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ከ145 ጥናትና ምርምሮች ፣ ከ125 በላይ የማህበረሰብ አገልሎቶች መሰጠት፣ ከተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር መሰል ተቋማት ጋር የትስስርና የአጋርነት ስራዎች መሰራታቸው ለዕቅዱ እንደመነሻ ያገለገለ ሲሆን። ከዚህ በተጨማሪም በዕቅድ አፈጻጸሙ ወቅት የታዩ ተግዳሮቶችና ውስንነቶችም በስፋት ተዳሰዋል። በተጨማሪም በዕቅድ ዝግጅቱ ላይ የዩኒቨርስቲው ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች ግምገማ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ባለድርሻ አካላት ፍላጎትን እና ከዩኒቨርሲቲው የሚጠብቁት ውጤት ያካተተ ግምገማ የተደረገበት ዕቅድ መሆኑ በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡ በዝግጅቱ ወቅትም የጥንካሬዎች፣ ውስንነቶች፣ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች ከመተንተናቸውም በተጨማሪ ዕቅዱን ለመፈጸም የሚያስችሉ (አስቻይ) እና የማያስችሉ (አደናቃፊ) ሁኔታዎች በዝርዝር ተለይተው መቅረባቸው በሪፖርቱ ተመላክቷል።

በእቅዱ ላይም ትኩረት የሚሹ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ተለይተው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ በዚህም መሰረት ዩኒቨርስቲው ለፐብሊክ ሴክተሩ የሚሰጣቸው አገልግሎቶችን ብቃት፣ ጥራት፣ ተገቢነትና፣ ተደራሽነት ማረጋገጥ ፤ የዩኒቨርሰቲውን አገልግሎት በኢንፎርሜሽን እና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) የታገዘ እንዲሆን ማድረግ ፤ ወጣት እና ሴት ሲቪል ሰርቫንቶችን ማብቃትና ተሳትፏቸውን ማሳደግ ፤ ከሀገራዊና ከዓለም አቀፍ መሰል ተቋማት ጋር ጠንካራ ትብብርና አጋርነት መፍጠር ፤ የዩኒቨርስቲውን ውስጣዊ አቅም በሰው ኃይል፣ በአሰራርና በአደረጃጀት ማጠናከር ፤ በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ሆነው ተቀምጧዋል።

የዩኒቨርሲቲው ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶችን በተመለከተም ዩኒቨርስቲው ወቅቱን ያገናዘበ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች እንዲኖረው እንዲሁም መሪ-ቃሉን እንዲፈትሽና እንዲያሻሽል ተደርጓል። በዚህም መሰረት የዩነኒቨርሲቲው ራዕይ "ፐብሊክ ሴክተሩን ከመገንባት አኳያ በ2022 በዘርፉ ከተሰማሩት ተቋማት መካከል የላቀ፣ በቴክኖሎጂ የዘመነና ተወዳዳሪ የአቅም መገንቢያ ተቋም መሆን" የሚል ሲሆን ይህን ራዕይ ለማሳካት በተልዕኮነት የተያዘው መሪ ሀሳብም "ፐብሊክ ሴክተሩ ውጤታማ የህዝብ አገልጋይ ሆኖ እንዲሰራ አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣ በስልጠና፣ በማማከር፣ በጥናትና ምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት" የሚል ሆኗል። ተገልጋይ ተኮር ፣ ፈጠራን ማበረታታት፣ ልቆ መገኘት፣ ዘለቄታዊ ውጤታማነት፣ ተባብሮ መሥራት፣ ብዝሀነትን መቀበል፣ ሁሌም መማር እና ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የሚሉት የዩኒቨርሲቲው እሴቶች ናቸው።

ስትራቴጂክ ዕቅዱ በአራት ዕይታዎች (Perspectives) የተቀመጠ ሲሆን ዕይታዎች የዩኒቨርሲቲውን አፈጻጸም ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር በተሟላ መልኩ ለማሳየት የሚያስችሉ እርስ በርሳቸው በምክንያትና በውጤት የተሳሰሩ ሲሆኑ ዩኒቨርሲቲውን ከተልዕኮውና ከራዕዩ በመነሳት ስትራጂያዊ ዕቅዱን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ዕይታዎቹ የተገልጋይ ተኮር ፣ የፋይናንስ፣ የውስጥ አሰራር እና የመማማርና እድገት እይታዎች በሚል ቀርበዋል።

በስትራጂያዊ ዕቅዱ ስድስት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች የተለዩ ሲሆን እነርሱም በትምህርት አገልግሎት የላቀ ውጤት ማስመዝገብ፣ በስልጠና አገልግሎት የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ፣በማማከር አገልግሎት የላቀ ውጤት ማስመዝገብ፣ በጥናትና ምርምር የላቀ ውጤት ማስመዝገብ፣ በማህበረሰብ አገልግሎት የላቀ ውጤት ማስመዝገብ እና የዩኒቨርሲቲው የውስጥ አቅም ግንባታ መሆናቸው ከቀረበው ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል።

ስትራቴጂክ ዕቅዱ በውስጡ አስራ አንድ የዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂያዊ ግቦች (Strategic Goals) የያዘ ሲሆን ከግቦች የሚጠበቅ ውጤትና የውጤት አመልካቾችም ተያይዘው ቀርበዋል። ግቦችም የተገልጋይ እርካታ ማሳደግ፣ የውስጥ ገቢን ማሳደግ እና የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማጎልበት፣ የትምህርት አገልግሎቶችን ማሳደግ፣ የስልጠና አገልግሎቶችን ማሳደግ፣ የማማከር አገልግሎቶችን ማሳደግ፣ የጥናትና ምርምር አገልግሎቶችን ማሳደግ፣ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ማሳደግ፣የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ስርዓት መዘርጋት፣ ብቃት ያላቸው፣ በስነምግባር የታነጹና የህዝብ አገልጋይነት መንፈስ የተላበሱ ወጣቶችና ሴቶችን በፐብሊክ ሴክተሩ ውስጥ ማፍራት፣ ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ተጠያቂ አመራርና አስተዳደር መፍጠር፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ተቋማት ጋር ያለንን ትስስርና አጋርነት ማጠናከርና ማስፋፋት፣ ናቸው።

ለስትራቴጂክ ዕቅዱም ዩኒቨርሲቲው በስትራቴጂያዊ ዘመኑ ትኩረት ሰጥቶ የሚያከናውናቸውን ግቦችና ተግባራት ለመፈጸም የሚያስችሉ የአፈጻጸም ስልቶችም የተዘጋጁ ሲሆን ዋና ዋና የአፈጻጸም ስልቶች ተብለው ከተለዩት መካከልም ጥናትን መሰረት ያደረገ እና ተገልጋይ ተኮር አገልግሎትን በመስጠት፤ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማረጋገጥ፤ የምንሰጣቸው አገልግሎቶች ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን የጠበቁ እንዲሆኑ በማድረግ፤ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ የታገዙ በማድረግ፤ ብቃትን ታሳቢ ያደረገ አገልግሎትን በመስጠት፤ በሰራተኞች መካከል አዎንታዊ የውድድር መንፈስ በመፍጠር፤ ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር፤ ተከታታይነት ባለው መልኩ የውስጥ አሰራርንና አደረጃጀትን ፍተሻ በማድረግና የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ፤ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ቤተሰባዊ ግንኙነት ለማጠናከር ፤የላቁ ሠራተኞችና አመራሮችን በመሸለምና እውቅና በመስጠት፤ ዩኒቨርሲቲው የሚያከናውናቸውን ስራዎች በቂ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ፤ ተከታታይነት ያለው የስኬትና የፋይዳ ግምገማዎችን በማካሄድ፤ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

ዩኒቨርሲቲው በስትራቴጂያዊ ዘመኑ እንደ ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategic Initiatives) ስድስት ፕሮጀክቶችን የያዘ ሲሆን እነርሱም የሰው ሀብት ልማት ማሻሻያ ፕሮጀክት፣ መሰረተ-ልማትና ፋሲሊቲዎችን የማስፋፊያና የማጠናከሪያ ፕሮጀክት፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋና አፃፃፍ ማበልፀጊያ ማዕከል/ English Language and Writing Center/



## አቶ ነስሩ አወል

*የእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር*



## አቶ ገብረትንሳይ ተስፋይ

*የየከተማ ማኔጅመንትና ትራንስፎርሜሽንና ስልጠናና ማማከር ማዕከል ዳይሬክተርና የስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ኮሚቴ ሰብሳቢ*

የማቋቋሚያ ፕሮጀክት፣ የስታቲስቲክስ ማዕከል /Statistics Center/ የማቋቋሚያ ፕሮጀክት፣ የውስጥ ገቢ ማመንጨትና ማልማት ፕሮጀክት፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ስርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት ሲሆኑ ዝርዝር የፕሮጀክቶቹ ማስፈጸሚያ በጀት፣ ስልትና መርሃ-ግብር አብሮ የተዘጋጀለት መሆኑ በሪፖርቱ ላይ ተጠቅሷል፡፡

የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈፃጸም መርሃ-ግብር  በተመለከተም በዕቅዱ ላይ ስትራቴጂክ  ግቦች፣  ዓላማዎች፣ ዋና ዋና ተግባራት፣ መለኪያ፣ መነሻ (Base Line)፣እና ዒላማዎች (Targets) የተካተቱ ሲሆን ዝርዝር የክትትልና የግምገማ ስልቱ በዕቅዱ ላይ ተመለካቷል፡፡ በ10 ዓመት የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዘመኑ የተነደፉትን ግቦች ለማሳካት በዩኒቨርሲቲው በአመራርና አስተዳደር፣ በትምህርት፣ በስልጠና፣ በማማከር፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎቶች ተግባራዊ ለሚደረጉ ስራዎች የሚውል የበጀት ፍላጎት ትንበያም በዕቅዱ ላይ ተቀምጧል፡፡

በሌላ በኩል ለሁለት ቀናት በዘለቀው የካውንስሉ ስብሰባው ላይም በ2013 ዓ.ም  ዕቅድና  በጀት ዓመቱ  የመጀመሪያ ግማሽ  ዓመት የስራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በአቶ ነስሩ አወል የእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር  ቀርቦ በካውንስሉ ሰፊ ውይይትና ግምገማ ተደርጎበታል፡፡ በቀረበው የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት መሰረት በበጀት ዓመቱ 1465 መምህራን፣ ኮንሰልታንት፣ ተመራማሪዎች እና የአስተዳደር ሰራተኞች  በስራ ላይ የነበሩ ሲሆን  5213 የነባር እና 2,569  አዲስ ገቢ የመደበኛ፣ የማታ እና የሳምንቱ መጨረሻ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተዋል፤ 1,903 ተማሪዎች ደግሞ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፡፡

በ2013 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዙ ግቦች እና ተግባራት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈጻጸም ጋር ተያይዞም የተገልጋይ እርካታ ማሳደግን በተመለከተ  የሰልጣኞች እርካታን 95 ከመቶ ለማድረስ ታቅዶ 90 ከመቶ ማድረስ  የተቻለ ሲሆን በፋሲሊቲና መስተንግዶ በሠልጣኞች የተገልጋይ እርካታ 95 ከመቶ ለማድረስ ታቅዶ 92 ከመቶ ማድረስ  ተችሏል ፡፡

የውስጥ ገቢን ማሳደግ እና የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማጎልበትን አስመልክቶም ከመማር ማስተማር ከተማሪዎች ምዝገባ፣ ከቅጣትና እና ከስራ ቅጥርና የደረጃ ዕድገት የፈተና አገልግሎቶችን ብር 18,966,655፤  ከስልጠና ዘርፍ ደግሞ ብር 20,312,500 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 13,997,164 መሰብሰብ ተችሏል፡፡ 4.7 ሚሊዮን ብር አገር አቀፍ የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲ ማርቀቅ ከፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመተባበር የተሰራ ምርምር ረቂቅ ቀርቧል ፤ ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በ3.7 ሚሊዮን ብር አገር አቀፍ የተገልጋይ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ውል በመፈራረም ስራው ተፈጀምራል፡፡ ከህትመትና ብዜት አገልግሎት ያልተጣራ ብር 1.3 ሚሊዮን ብር እንዲሁም  በICT ስልጠና 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር )የውስጥ ገቢ ማመንጨት ተችሏል፡፡

የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የቋሚና የአላቂ ንብረት ቆጠራ ተከናዉኗል፡፡  በIFMIS ሥርዓት የበጀት አጠቃቀም በመከታተል ወቅታዊ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት የቀረበ ሲሆን በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በተደረገ ግልጽ ጨረታ  አንድ ተሽከርካሪ  በብር 200,000 እና ከ1,100 ባዶ ጀርካን ሽያጭ በጠቅላላ በብር 207,865 /ሁለት መቶ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ስድሳ አምስት/ ማግኘት ተችሏል ፡፡

በበጀት ዓመቱ ከመንግስት ከተፈቀደው ከመደበኛ በጀት ብር 282,727,200 ውስጥ ብር 75,156,012.79 (26.58%) ፣ ከውስጥ ገቢ ከብር 48,026,900 ውስጥ ብር 15, 116,290.96 (31.47%) ፣ ከካፒታል በጀት ከብር 180,000,000.00 ብር ውሰጥ ብር  48,095,110.34 (26.72%) ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን በጠቅላላው ከተፈቀደው በጀት ከብር 510,754.100 ውስጥ ብር 138,367,414.09 (27.09%) ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገ ሲሆን በቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎባቸው ያልተወራረዱ ብር 21,145,847.63 ሲወራረድ አጠቃላይ የበጀት አጠቃቀሙን 41.40% ይደርሳል፡፡ የግማሽ ዓመት በጀት አፈፃፀሙ ዝቅ ማለት በኮሮና ቫይረስ ምክንያት መማር ማስተማሩና ስልጠና በሙሉ አቅም መተግበር አለመቻሉ እንደሆነም በሪፖርቱ ተጠቅሷል፡፡

የፐብሊክ ሰርቪሱን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ጥራት፣ አግባብነትና ተደራሽነት ያለው ትምህርት ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሰረትም አራት ስርዓተ-ትምህርቶች  ተቀርጸው  ማለፍ  የሚገባቸውን  ሂደቶች  አጠናቀው በሰኔት ለማጸደቅ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ የኮቪድ-19 ፕሮቶኮልን ታሳቢ ያደረገ የመጀመሪያ ዙር ተማሪዎች የመቀበል ስራ ተከናውኗል፡፡ ያለፈው የትምህርት ዘመን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በመስተጓጎሉ የሴሚስቴር ስራውን ለማጠናቀቅና የማጠቃለያ ፈተናውም በኦን ላይን እንዲሁም እንደአመቺነቱ በተማሪዎችና በመምህራን ስምምነት በኦንላይን ወይም በገጽ ለገጽ የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2012 ዓ.ም የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም (HDP) ሲከታተሉ የነበሩ 96 መምህራን ፕሮግራሙን በሚገባ ተከታትለው ያጠናቀቁ ሲሆን በ2012 የትምህርት ዘመን በተለያዩ ምክንያቶች ሳይመረቁ የቀሩ 207 ተማሪዎች እንዲመረቁ ተደርጓል፤ የትምህርት ድጋፍ (Tutorial) የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተለይተው ኮሌጆች የትምህርት ክፍሎችን በማስተባበር አገልግሎቱን እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡

በቤተ-መጽሐፍትና  በሬጅስትራር  ለሚሰጡት  አገልግሎቶች  የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድን የተከተለ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን  3,063 የኤሌክትሮኒክስ   መጻሕፍትን   የዩኒቨርሲቲውን   ስርዓተ-ትምህርት መሰረት በማድረግ የተለያዩ ነፃ ዳታ ቤዞችን በማፈላለግና በማውረድ እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲው የዲጂታል ሲስተም ሰርቨር ጋር በማገናኘት ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገዋል፣ የኤሌክትሮኒክስ መጻሕፍቶቹ በዋጋ ሲተመን  ብር 2,600,000 (ሁለት ሚሊየን ሰድስት መቶ ሺህ ብር) እንደሚሆን የቀረበው የግምገማ ሪፖርት አመላክቷል፡፡

ከ1,723 የፒኤችዲና የማስተርስ ተማሪዎች የመመረቂያ ፅሑፍ በኤሌክትሮኒክስ ፎርም በመቀበል 786 የሚሆኑትን ወደ ዲስፔስ ሲስተም እንዲገቡና ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርጓል። ዩኒቨርሲቲው የአመታዊ ክፍያ የሚከፍልባቸው 31 የጆርናል ዳታቤዞች ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

የሰው ሀይል የመፈፀም አቅም የሚያጎለብቱ የስልጠና አገልግሎቶችን ለማሻሻል በተያዘው ዕቅድ መሰረት ለ812 ሰልጣኞች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን 36 የስልጠና ሞጁሎች ብቃትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንደገና ተዘጋጅተዋል። የብቃት- ተኮር ክፍተት ልየታን መሰረት በማድረግ 35 የሽግግር ጊዜ ሥልጠናዎች ተለይተዉ ሞጁሎች ተዘጋጅተዋል። Internship Based የሆኑ ስልጠናዎችን በመለየትም ሀገር- አቀፍ የብቃት ሰርቲፊኬት መስጠት የሚያስችል ጋይድላይን ተዘጋጅቷል። 16 ሞጁሎች የጥራት ማረጋገጫ ቡድን በተዘጋጀው የብቃት-ተኮር ሞጁል ማዘጋጃ መመሪያ መሠረት ስለመዘጋጀታቸው በተዘጋጀው መገምገሚያ መስፈርት መሠረት ተገምግመዋል። ፍላጎትና ብቃትን መሰረት ያደረገና ተደራሽነትን የሚያሰፋ የስልጠና አገልግሎት ከመስጠት አንፃርም ተገልጋይ ተቋሙ በአመቻቸው የስልጠና ቦታና በጠየቁት የሥልጠና ርዕሶች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፤ ጥራትን ከመጠበቅ አንጻር የሚዘጋጁ የስልጠና ሞጁሎች በጥራት ቡድን እየተገመገሙ እንዲያልፉ ተደርጓል። አሰራርንና አደረጃጀትን የሚያጎለብቱ የማማከር አገልግሎቶችን ለማሻሻል በተደረገው ጥረት የአሰሳ ከተማ እና የጋንቤላ ከተማ መዋቅራዊ ፕላን ተጠናቆ ርክክብ ተከናውኗል፤ 9 የማማከር ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል።

በበጀት ዓመቱ የጥናትና ምርምር አገልግሎቶችን ለማሳደግ በተያዘው ዕቅድ መሰረትም በምርምር ማዕከላት አማካኝነት 6 የምርምር ንድፎች የዝግጅት እና የውስጥ የግምገማ ሂደት ተጠናቆ መረጃ የማሰባሰብ ስራ ለማስጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛል። አገር አቀፍ የፖሊሲ ግብዓት ሊሆን የሚችል አንድ የምርምር ፕሮጀክት የመጀመሪያውን ምዕራፍ ተጠናቆ ለምርምር ለማቅረብ ዝግጁ ተደርጓል። 47 የምርምር ንድፎች በግልና በቡድን ለመስራት በ56 የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎች ቀርበው በዝርዝር የመገምገምና ተገቢነታቸውን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶ ተመራማሪዎች ከመስክ መረጃ የመሰብሰብ ስምሪት ላይ ይገኛሉ።

የሀገር አቀፍ አገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲ ቀረጻ ምርምር ድራፍት ተጠናቆ ለግምገማ ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቧል። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት አንደምታ የምርምር ስራ የመጀመሪያው እርከን ተጠናቆ ለህትመት በቅቷል። የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ መዋቅራዊ ተገቢነት የሚፈተሽበት ጥናት የመጀመሪያው ዙር ተጠናቋል፣ ከፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በትብብር የተከናወነው አገር አቀፍ የተገልጋይ እርካታ ጥናት እና የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲም ተጠናቆ የመጀመሪያ ረቂቅ ርክክብ የተደረገ ሲሆን ከኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ጋር ውል በመግባት አገር አቀፍ የተገልጋይ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ከመስክ መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተጠናቋል።

በ2012 በጀት ዓመት የተጀምሩ 4 ምርምሮች ተጠናቀው በሚካሄደው የምርምር ወርክሾች ለማቅረብ ዝግጁ ተደርገዋል ። በዩኒቨርሲቲው የምርምር አበልፅጎት ማዕከልን አገልግሎትን ለማሳደግ የግብዓትና ሰው ሃይል የማሟላት ስራ እየተሰራ ጎን ለጎን ስራውን እንዲጀምር ተደርጓል። ከ2008 እስከ 2012 በጀት አመት የተከናወኑ የጥናትና ምርምር ውጤቶች በመረጃ ቋት በአግባቡ እንዲደራጁ ተደርጓል።

የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ማሳደግን በተመለከተም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ሬድዮ በግማሽ ዓመቱ ሊያሰራጨ ካቀደው የ935 የሰዓት ስርጭት የ925 ሰዓት የፕሮግራም ስርጭት ማስተላለፍ ተችሏል። ዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ በማህበረሰብ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚዲያ ደርጋቸውን አካላትና ፍላጎታቸውን በዳሰሳ ጥናት የመለየት ስራ ተሰርቷል። በማህበረሰብ አገልገልግሎት መስክ 20 የማህበረሰብ አገልግሎት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 13 ለመስጠት ተችሏል።

የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ስርዓት መዘርጋት የሰው ሀብት ብቃት የምዘና እና ሰርቲፊኬሽን ማዕከል ማቋቋያ መመሪያና የመዋቅር ጥናት የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል። በሶስት ደረጃዎች የብቃት ሰርቲፊኬት ለመስጠት መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል። የሽግግር ጊዜ የሥልጠና ሞጁሎች ተዘጋጅተዉ ወደስራ ተገብቷል። የሚሰጡ ስልጠናዎች በደረጃ ተመድበዉ ለፌደራል ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተላከ ሲሆን ለተግባራዊ ልምምድ የመተግበሪያና የሰልጣኝ መመደቢያ መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል። የምዘና ሰርተፍኬሽን ማዕከል ህንጻ ግንባታም በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ተጠያቂ አመራርና አስተዳደር ከመፍጠር አኳያም ዩኒቨርሲቲው በመደበኛ ፕሮግራም በሁለተኛ ዲግሪ 829 እንዲሁም በማታ፣ በቅዳሜና እሁድ ፕሮግራም በሁለተኛ ዲግሪ 1,074 በአጠቃላይ 1,903 ተማሪዎችን ማስመረቅ የቻለ ሲሆን ለመምህራን በተሰጠው የደረጃ ዕድገቶችም በትምህርት ማሻሻል 4 ወደ ረዳት ፕሮፌሰርነት እና በደረጃ ዕድገት 2 መምህራን ከሌክቸረር ወደ ረዳት ፕሮፌሰር እና 2 ከረዳት ፕሮፌሰር ወደ ተባባሪ ፕሮፌሰርነት እንዲያድጉ ተደርጓል። በSelf User አጠቃቀም ላይ በኦንላይን ለ78 ሰራተኞች በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ስልጠና ተሰጥቷል፤ 10 የአስተዳደር ሠራተኞች የደረጃ እድገት እንዲያገኙም ተደርጓል። በአስተዳደር ዘርፍ በወጡ ክፍት የስራ መደብ ማስታወቂያ መሰረት 162 ባለሙያዎች ቅጥር ተፈጽሟል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ግኝቶች መሠረት የ2011 በጀት ዓመት በቁጥር ደረጃ ከተገለፁት የአሰራር ክፍተቶች ውስጥ 98% እርምጃ የተወሰደበት ሲሆን ቀሪው 2% ላይ እርምጃ ለመውሰድ ከፌደራል ኦዲተሮች ጋር ውይይት እየተደረገ ይገኛል፤ የ2012 በጀት ዓመት ኦዲት በመደረግ ላይ ያለ ነው። የዩኒቨርሲቲውን የሰራተኞችና ሀላፊዎች የስነምግባር መመሪያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፤ 1313 ሰራተኞች የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ተካሂዷል። የዩኒቨርሲቲውን ላንድስኬፕ ዲዛይን የማሻሻል ስራ ተሰርቷል።



ከሀገር ውስጥና ከውጭ ተቋማት ጋር ያለን ትስስርና አጋርነትን ማጠናከርና ማስፋፋት በተመለከተም ከከተማ ልማት እና ኮንስተራክሽን ሚኒስቴር ጋር የልህቀት ማዕከልነት መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በጋራ የሚሠሩ ሥራዎች የተለዩ ሲሆን የህግ ት/ቤት ከግሪዝ ዩኒቨርሲቲ ኦስትሪያ ካለው ጋር ትስስር ቀጥሏል። በሕግ ት/ቤት ስር ለሚከፈቱ ሁለት አዳዲስ ፕሮግራሞች ተቋማዊ ድጋፍ እንዲሰጥ ከፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግና ከፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጋር ግንኙነት ተፈጥሯል። ከኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት እና ከሆፕ ዩኒቨርሲቲ ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ወደ ስራ ገብተናል። ዩኒቨርሲቲው ከገቢዎች ሚ/ር፤ ከገንዘብ ሚ/ር፤ ከመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በአጋርነት በመስራት ላይ መሆኑ በሪፖርቱ ተመላክቷል።

በቀረበው የአስር ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድና በ2013 የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የስራ ዕቅድ አፍጻጸም ላይም የካውንስሉ አባላት በስፋት ተወያይተዋል። አባላቱም በቀሪው የበጀት ዓመቱ የስራ አፈጻጸም ላይ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡና ሊሻሻሉ ይገባሉ ያሏቸውን ሀሳቦችና አስተያየቶች ያቀረቡ ሲሆን የዩኒቨርሲቲውን ዕቅድ ለመተግበርና ወደ መሬት በማውረድ ለተቋማዊ ስኬት መሳካት በጋራ መስራት እንደሚገባም አስምረውበታል።

# RES PLC የአፍና አፍንጫ ጭንብል ልገሳ አደረገ



የ Reliable Educational Materials Supplier Plc የተባለ ተቋም 5000 የአፍና አፍንጫ ጭንብል ለኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ አበረከተ። በርክክቡ ወቅት አቶ ገብረ ሐዋርያ ገ/መድህን የአስተዳርና ተማሪዎችአገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት እንደተናገሩት ይህ ተቋም በፈቃደኝነት ድጋፍ ስላደረገልን በዩንቨርሲቲዉ ስም ምስጋናዩን አቀርባለሁ። በአሁኑ ወቅት ተማሪዎቻችንን ተቀብለን ትምህርት የጀመርንበት ወቅት በመሆኑ ለተማሪዎቻችን በተቻለ መጠን ለማዳረስ እንጥራለን ብለዋል። በተጨማሪም ይህን ድጋፍ በይበልጥ ወደተቋማችን እንዲመጣ ላስተባበሩልን ዶ/ር ገነት ዘዉዴ ምስጋናዩን አቀርባለዉ በማለት ከተቋሙ የተለገሰዉን የአፍና አፍንጫ ጭንብል ተረክበዋል።



ተቋሙን ወክለዉ ድጋፉን ያበረከቱት አርሀንት ባፋና እንዳሉት ወደፊት አቅም በፈቀደ መልኩ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸዉን በመግለጽ ወደፊት ከዩንቨርስቲዉ ጋር በጋራ ብዙ ስራዎችን በትብብር ለመስራት ፈቃደኝነታቸዉን ገልጸዋል።






**International and Public Relations Coordination Directorate**

**Contact Address:**

Tel.0116 46 2887,Extension: 253/252/257 , Fax: 0116463016

P.O.Box5648, E-mail: www.Iprd @ecsu.edu.et ,

Website: www.ecsu.edu.et, Tweeter: @ECSU tweets ,FM Radio:-100.5MHz

Facebook: Ethiopian Civil Service University





BUILDING CAPACITIES IN PUBLIC SECTOR SINCE 1995


PRINTED BY *International & Public Relations Directorate*